 

# ልፋፈ ጽድቅ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ሐምሌ 18 ቀን 2013 ዓ/ም

nigatuasteraye@gmail.com

“ጸሐፎ ውስተ ምርፋቀ ጥኀተ አብያቲከ ወውስተ ዴዴያቲከ። መሀሮ ወንግሮ ለወልድከ እንዘ ትነብር በውስተ ቤትከ ወእንዘ ተሐውር ውስተ ፍኖትከ ።ወለእመ ሰከብከሂ ወተንሣእከሂ ይኩንከ ትእምርተ ዘኢይትሀወስ እምቅድመ አዕይንቲከ” (ዘዳ 6፡7__9 ) ።

ልፋፍ ማለት ጽሑፍ ማለት ነው። ከጽድቅ ጋር ሲገናኝ ልፋፈ ጽድቅ ተብሎ ይነበባል። ወደ በጎ ተግባር የምትመራ የእውነት ጽሑፍ ማለት ነው። ልፋፈ ጽድቅ መሠረቷ ከላይ የሰፈረው የኦሪቱ ቃል ነው። በውስጧ የተሸከመችው የዚህን ዓለም አላፊነት እና የመንግስተ ሰማይን ዘላለማዊነት የሚገልጽ ነው። በብራና ተጽፋ ተደጉሳ በማህደር ሆና መነኮሳት ባንገታቸው አጥልቀው በክብር ይይዟታል። በቤትም በመንገድም ሲቀመጡም ሲነሱም ይደግሟታል። የየእለቱን ድካማቸውን እያዩ ራሳቸውን ያስተካክሉባታል። ሲሞቱም አብራ ትቀበራለች። በይዘቷ በቤተ ክርስቲያናችን ካሉት መጻሕፍት ሁሉ ያነሰች ናት።

እኔም በዚህ ዘመን የገጠመንን ፈተና ሳንወጣ ማድረግ የሚገባንን ሳናደርግ ሞት እንዳይቀድመን ለማሳሰብ ይህችን ልፋፈ ጽድቅ በ 7 አናቅጽ ከፍየ በማዘጋጀት በዚህ ዘመን ለምንገኝ ካህናት በተለይም ለጳሳት ይልቁንም ለቅዱስ ፓትርያርካችን አቀረብኋት።

1ኛ፡-

ለብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርካችን

ለብጹዐን አቡኖቻችን

እንደኔ ላላችሁ ካህናት

ምንም እንኳ የሰው ልጅ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት ከገነት ጀምሮ ፍጹም ቅዱስ ባለመሆኑ ያለ አንዳች እንከን በዚህች ምድር ያለፈባት ትውልድ ባይኖርም፤ በኢትዮጵያና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ባረመኔ ወያኔዎች የደረሰው ጸዋትወ መከራ፤ እንኳን በኢትዮጵያ በሌሎች አገሮች ይፈጸማል ተብሎ የማይታሰብ ነው።

የኢትዮጵያ ምድር ለ30 አመታት ወያኔወች በገደሏቸው በኢትዮጵያውያን ሬሳ ተሸፈኗል። የኢትዮዮጵያ ሰማይም በደም ግምጃ ተጋርዷል። የኢትዮዮጵያ ምድርም በልጆቿ የደም ጎርፍ ታጠቧል። በኢትዮጵያ የሚነፍሰው ነፋስም በሞተው ሰው ሬሳ ሽታ ተበክሏል። የሞት ጢስ ተሸክሞ በመላ ኢትዮጵያ የሚነፍሰው ነፋስ የሞት ስርቅታና ትንታ የሚያነጥስበት ይህን የመሰለ ክፉ ዘመን ተከስቶ አያውቅም።

ኢትዮጵያ አገራችን ሲዋጌት እሷም ስትዋጋቸው ለኖሩት አውሮፓውያን ተገዳዳሪዎቿ በወያኔ ተግባርና በፓትርያርካዊ ንግግር ተላልፋ የተሰጠችበት ይህን የመሰለ ዘመን ተከስቶ አያውቅም። ቤተ ክርስቲያናችንንም በስነ መለኮት ትርጓሜዋና በቀኖናዋ በምታወግዛቸው ሰባኪወች የተወረረችበት፤ በምእመናኖቿ ላይ የደረሰውን መከራ በሩቅና በቅርብ ላለው ሰሚ እንዳታሰማ የታፈነችበት የወላድ መካን የሆነችበት ከነበራት ግርማ ሞገሷም ዝቅ ብላ የታየችበት እንዲህ ያለ ዘመን አልገጠማትም።

አንዱ የሌላውን ብሶትና ጩኸት ሰምቶ እርስ በርሱ እንዳይረዳዳ የኢትዮጵያን ህዝብ አለያይቶ፤ አከፋፍሎ አራርቆና አቆራርጦ የገደለው ወያኔን የመሰለ ጠላት በታሪካችንም የለም።

ቅዱስ ፓትራያርካችን ሆይ ! እርሰዎና ባመራረዎ ስር ያለን እኛ የዚህ ዘመን ካህናት ሁላችን ፤ እናቱ ገበያ የሄደችበት ህጻን በሚያለቅሰው ማለዝን በምንለው ነገረ ዘርቅ በህዝቡ ዋይታና ልቅሶው ላይ ተሳለቅንበት።

በኛ ተስፋ የቆረጠው ይህ ትውልድ ወያኔዎች እንዳይገናኝ የጋረዱበትን የክልል አጥር አፈራርሶ፤ ያሰሩበትን ሰንሰለት በጣጥሶ አንዱ የሌላውን ድምጽ እየሰማ ነው። በእኛ አውደ ምህረቱ ቢታፈንበትም፤ እርስ በርሱ እየተጠራራ የጋራ ብሶቱን ለዓለም እያሰማ ነው። በቅዱስነተዎ አመራር ስር ያለን እኛ ካህናት ግን በቅዱስነተዎ ዝምታ በመታገዳችን "ለንጹሐን ካህናት አገልጋዮችህ በምድር ላይ ኃጢአትን ያስሩ ዘንድ የበደልን ማሰሪያ ይፈቱ ዘንድ የክህነትን ተልእኮ የሰጠህን" (37) ብለን በህዝብ ፊት የምናነበውን በተግባር ለማዋል አልቻልንም።

የፓትርያርክነቱን ሀላፊነት በአምላክና በህዝብ ፊት ምለው ሲቀበሉ የገቡትን ቃል ለመፈጸም ሽፋፍነው ከመናገር ተላቀው፤ "አፍቀርኩ ጽድቀ ወአመጻ ጸላእኩ" የሚለውን የእግዚአብሄርን ፈቃድ በመከተል አመጻኛውን በግልጽ ያወግዙ ዘንድ፤ በስመዎና በሰውነተዎ የተቀዳጇቸውን ነዋየ ቅድሳት ለመፈራረጃና ለዚህች ልፋፈ ጽድ መረጃ ይሆኑ ዘንድ ከዚህ በታች ያቀረብኳት እውነተኛ ምስክር (ልፋፈ ጽድቅ ) እነሆ ! !

## 2ኛ፡-ብጹዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን ሆይ !



ለሰው ፊት ሳያዳላ በያንዳንዱ ላይ እንደስራው የሚፈርደው አምላክ "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ"ባለን መሰረት ሁላችንም ቅዱሳን ብንሆንም፤ ከገጠሙን ተደራራቢ የኃጢአትና የበደል ብክለት እንነጻ ዘንድ ብጹዓን የሚባሉትን አቡኖችንና እኛን ካህናቱን በማስተባበር የህጽበተ እዱን ስርአት የማስፈጸሙ ሀላፊነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት) የመዋጊያ መሳሪያ የሚባሉትን (ንዋየ ሀቅል) በስመዎ ደራርበው ተሸከመዋል።

ሀ፡-በምንኩስናዎ በገዳማት ላሉት መነኮሳት አበምኔታቸው

ለ፡-የመላ ኢትዮጵያውያን ፓትርያርክ

ሐ፡-ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት (የብጹአን ጳጳሳት መሪ)

መ፡-የሲኖዶስ ሊቀመንበር

ሠ፡-የደብረ ሊባኖስ እጨጌ

ረ፡-የአኩስም ሊቀ ጳጳሳት

ሰ፡-በአዲስ አበባ ከተማ ላሉት ሁሉ አድባራት ሊቀ ጳጳስ

"ይትፌሣህ ከመ ያርብህ ዘይሜርድ ፍኖቶ" (መዝ 18) እንዲል፡- ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት በስመዎ ከተሸከሟቸው መንፈሳውያን የጦር ትጥቆች ጋራ፤ ከራስ ጸጉረዎ እስከ ጥፍረዎ በመላ ሰውነትዎ የተሸከሟቸውን መንፈሳውያን የመዋጊያ ምልክቶችን እገልጽለወታለሁ።

ሀ፡-በራስዎ <u>ጌራ መድኃኒት</u> (የራስ ቁር) <u>ደፍተዋል</u>

ለ፡-በትከሻዎ የአርበኝነትን የወርቅ ለምድ <u>ደርበዋል</u>

ሐ፡-፡-ከራስዎ እስከ ትከሻዎ የወረደውን ቀጸላ <u>ተቀዳጅተዋል</u>

መ፡-በቀኝ እጅዎ መስቀሉን <u>ጨብጠዋል</u>

ሠ፡-በግራ እጅዎ አርዌ በትር <u>ይዘዋል</u>

ረ፡-ይባርኩኝ አባቴ እያለች ከልጆቿ አፍ ተሻምታ በመቀነቷ የቋጠረቻትን ሳንቲም ለቤተ ክርስቲያን መባ የምትሰጠው እናት በጫካ ወልዳ ከነ ልጇ የጅብ ራት ስትሆን፤ ቅዱስነተዎ በሰጠችው መባ የቅጥሯ መሠረት በከበረ ድንጋይ፤ ግርግዳዋ በኢያሰጲድ ሰንፔር፤ ወለሏ በመርግድ ቢረሌ ፤ ጣሪያው ብርጭቆ በሚመስል ንጥረ ነገር በተሰራ ጽርሀ መኖረዎ ለዚህ ጊዜ እንዲቆሙላት ነበር።

ቡራኬዎን የሚናፍቀው አባ ወራ ቤቱ ፈርሶበት በጫካ በዱር የሌሊቱ ቁርር የቀኑ ሐሩር እየወረደበት ሳለ፤ ቅዱስነተዎ ግን ከመንበርዎ ታጅበው ብዙ ነዋየ ወደፈሰሰበት የክብር መኪና እስክደርሱ ድረስ ጫማዎቸዎን አፈር እንዳይነካቸው እጅግ ውድ በሆነ በወላንሳ ሥጋጃ ላይ የሚኄደዱት ይህን የመሰለ መከራ ሲደርስበት በሩቅና በቅርብ ላለው ሁሉ ታዛቢ ባንደበተዎ እንዲመሰክሩለትና አስፈላጊም ከሆነ ተላልፈው እንዲሞቱለት ነበር።

ሰ፡-ከእርሰዎ በፊት የነበሩት አቡነ ተክለ ሃይማኖት፤ አቡነ መርቆርዮስና፤ አቡነ ጳውሎስ ወደ መንበረ ፓትርያርክነቱ ሲገቡ የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለማጥናት እንደርሰዎ ፓትርያርካዊ የተከማቸ የስራ ልምድ አልገጠሟቸውም። እርሰዎ ግን ይህን ያህል የስራ ልምድ እያለዎት የተረከቡትን መንበር ይዘው ፓትርያርካዊ ሀላፊነተወን ባለመጣተዎ ሐዋርያዊቷ ትውፊት ወደቀች።

## 3ኛ፡-የወደቀችው ሐዋርያዊት ትውፊት

በሐዋርያት ዘመን ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላወች ጠማማ ነገር የሚናገሩ አንደበተኞች በህዝብ መካከል ተከሰቱ። ህዝቡን ለሞት አደጋ የማይዳርገውን ግርዘትን እየጠቀሱ "ካልተገረዛችሁ ጠፋችሁ" እያሉ በህዝቡ መካከል ሽብር የሚፈጥር ወሬ አሰራጩ። የህዝቡን ስሜት ቀስቅሱት። ሐዋርያት ግን አንደበተኞች አጉልተው ባቀረቡት ተራ ነገር ሳይጠለፉ በህዝቡ ህይወት ላይ አደጋ በሚያመጡ ዓበይት ነገሮች ላይ አተኮሩ። ይልቁንም አንደበተኞች ያላዩዋቸው ለጤና ለሰላም ጠንቅ የሆኑ መከረና ስቃይ አዝለው በማንዣበበ ላይ የነበሩት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አደጋዎች ነበሩ።

ሀ፡-የታነቀ መብላት፤ ማለትም ሞቶ የተገኘ በህዋሳት የተበከለ

ለ፡-ዝሙት ማለትም ኃጢአትን በገዛ ሰውነት ላይ መቅረጽ

መ፡-ለጣዖት የተሰዋ መብላት ማለት የራስን መንፈስ በርኩስ መንፈስ ማስገዛት

ሠ፡-ደም መጠጣት ማለትም አራዊት አለመሆን

ሐዋርያት "ኢንጸመድ ማእዳተ አላ ለ መልእክተ ቃሉ" ብለው ከሥጋዊ ጥቅም ከገንዘብ ራሳቸውን ጠብቀው፤ አንደበተኞች በፈጠሩት ውዝግብ ግራ ሳይጋቡ በህዝቡ ላይ ያንዣበቡትን አደጋወች ተመለከቱ።

ህዝቡን እየከፋፈሉ የሚያናውጡትንና በህዝቡ ላይ ውዝንብር የሚረጩትን "አንዳንድ ሰዎች ያለኛ ፈቃድ በንግግራቸው ልባችሁን እንዳወኩና እንዳናወጧችሁ ሰምተናል" የሐዋ 15 ፡24 በማለት ገስጸው፤ ከተዘረዘሩት ከአራቱ ነገሮች ብቻ ብትርቁ ለጤንነታችሁና ለሰላማችሁ መልካም እንደሚሆንላችሁ "እኛና መንፈስ ቅዱስ ወሰንናል" ብለው ለህዝብ የሚበጀውን ወስነው አወጁ።

ይህች  ትውፊት እርስዎን በመሳሰሉ ፓትርያርኮች እየተመራች ዓለም እስከታልፍ ድረስ በምድር ላይ የምትቀጥለው ቤተክርስቲያን የምትፈጽመው ለሁላችንም በርሰዎ መሪነት እንድንፈጽማት የተሰጠችን ያደራ ተልእኮ ትውፊታችን ነበረች።

ሐዋርያት የገጠሟቸውን እንቅፋቶች ለመፍታት ያስገደዳቸውን ህዝባዊ ፍቅርና ሀላፊነት በእኛ ላይ ከሚታየው ህዝባዊ ፍቅርና ሃላፊነት ጋራ ስናነጻጽረው በኛ ላይ የሚታየው ህዝባዊ ፍቅርና ለህዝብ ማሰብ በእንስሳት መካከል ከሚታየው መተሳሰብ በታች ወደቀ። በሀዋርያት ዘመን የተከሰቱትን እንቅፋቶች በኛ ዘመን ከተከሰቱት መሰናከሎች ጋራ ስናነጻጽራቸው፤ በኛ ዘመን በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሱት ትዕይርቶች በብዛታቸውና በክብደታቸው እጅግ የከፉ ወደርና አማራጭ የሌላቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

ሀ፡-በተለያዩ ኢትዮጵያ አስተዳደሮች አማርኛ መናገር።

ለ፡-ኢትዮጵያዊ መሆን

ሐ፡-ኦርቶዶክስ ክርስቲያን መሆን

መ፡-አማራ ሆኖ መወለድ

ሠ፡-ከሀ እስከ መ ከተዘረዘሩት ማንነቶች ጋራ መነካካት

ወያኔዎች እነዚህ አምስቱንም ማንነቶች አሟልቶ የተገኘውን ሁሉ በማደን፤ በቢለዋ እያረዱ፡ በጦር እየወጉ፡ ዘሩ እንዲጠፋ ሲያደርጉ፤ በርሰዎ ፓትርያርካዊ አመራር ስር  የምንገኝ ሁላችን የህዝቡን ዋይታና እንባ ልንካፈል፤  ችግሩን ልንቀርፍለት ቀርቶ ድምጹን እንዳያሰማ ታራሚ በምትለው በወያኔ ማፈኛ ቃል አሸማቀቅነው። ታራሚ እያለ ሲያስረው ሲገድለው ከኖረው መንግሥት ጋራ በመተባበር ቤተ ክርስቲያናችን ድምጿን ለህዝቧ እንዳታሰማ ሁላችንም ተባብረን አፈናት። አባቶቻችን ጵጵስናን ከውጭ ዜጋ አላቀው በተወላጆች ኢትዮጵያውያን ትከሻ ላይ እንዲያርፍ የጣሩት ይህን የመሰለ አደጋ ኢትዮጵያን እንዳይገጥማት ነበር። ጥረታቸውን ሁሉ ከንቱ አደረግንባቸው።

## 4ኛ፡-አባቶቻችን ጥረው ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት ከንቱ የሆነው ጵጵስና



አውሮፓውያን ኢትዮጵያን ወረው እናቶችን ከነ ልጆቻቸው ሲገደሉ፡ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥሉ፡ አርበኞች በዱር በገደል በገጠር በከተማ ተሰማርተው ሲታገሉ፡ እነ አቡነ ጴጥሮስ በመትረየስ ሲረሸኑ፤ መምህር ገ/ኢየሱስን የመሳሰሉ ሊቃውንት በህዝባቸውና በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የነደደው እሳት ከህዝባችን በፊት እኛን አመድ ያድርገን በማለት በህዝባቸው ፊት ሲቃጠሉ፤ ግብጻዊው ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ጣሊያን ሂደው በዚያው ወደ አገራቸው ወደ ግብጽ እንደሂዱ ሳይመለሱ ቀሩ።

ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በሰላም ጊዜ ከአገር ተወላጁ በላይ አገራችን በምታፈራው ሥጋዊ ጥቅም ተንደላቀው ሲኖሩ፤ በመከራ ጊዜ ከህዝቡ ጎን ባለመቆማቸው እንጅ፤ አባቶቻችን የጵጵስናን ሀላፊነት ከውጭ ዜጋ አላቀው ወደ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን እንዲሻገር ያደረጉት እንደወያኔወች ዘረኞች ጎጠኞች ሆነው አልነበረም።

ልውላነ አዕምሮ የነበሩት አባቶቻችን የፖለቲካውን አመራር በባእድ ሳያስነኩ መንፈሳዊውን አመራር ብቻ ለውጭ ዜጎች የለቀቁት፤ በምንኩስና ላይ የተጫነው ጵጵስና ከምናኔው ጋራ የተጣበቀ ነው። ከዘር ከጎሳ ከንብረት የተላቀቀ መንፈሳዊ ልዕልናውን በጥቅማ ጥቅም የማያዋርድ ነው። ብለው በማመን እንጅ ሞኞች ወይም ግብጻውያንን ማባረር ተስኗቸው አልነበረም።

በባእድ ዜጋ ላይ ተጭኖ የመጣው ጵጵስና የኢትዮጵያን ልጆች ከፉ ዘመን ሲገጥማቸው መካዱና ከጠላት ጋራ መሰለፉ "እመቦ ዘይተሉ ኖላዌ እኩየ ሞቱ ከሡት በቅድሜሁ" (ፍ አ 5፡149) የሚለውን ቀኖና በጥልቅ እንዲመለከቱት

አባቶቻችንን አስገደዳቸው። ይህም " ጊዜ አይቶ የሚከዳውን ጳጳስ ብጹዕና ቅዱስ እያለ የሚከተል ክርስቲያን ሞት ከበሩ ይጠብቀዋል" ማለት ነው።

በሌላ ዜጋ ላይ ተፈናጦ የመጣው ጵጵስና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መከራ ሲመጣበት ሊጋረድለት ሊሞትለት ቀርቶ፤ አካሉንና ድምጹን ከህዝቡ ሰርቆ ከሞሶሎኒ ጋራ ሮም ላይ ብቅ ማለቱ አባቶቻችንን ተስፋ አስቆረጣቸው።

ዛሬስ ምእመናን እየተሳደዱ በሰይፍ ሲታረዱ በጦር ሲወጉ በጥይት ሲረሸኑ የቤተ ክርስቲያን ህንጻወች ሲቃጠሉ ከግብጻውያን ወደ አገር ልጆች የተላለፈው ጵጵስና ምን እያደረገ ነው? አካሉንና ድምጹን ከህዝቡ ሰርቆ ከባእድ ምንደኛ ጋራ ተሰልፎ ታፈንሁ ከማለትና የህዝቡን መጨፍጨፍ ቁጭ ብሎ ከመመልከት በቀር ከግብጻዊው ጳጳስ ምን የተሻለ ነገር አደረገ? የሚል ጥያቄ በኢትዮጵያውያን መካከል የወይይት ርእስ ሆኗል።

ታዲያ ጵጵስናውን ታግለው ያመጡት አባቶቻችንስ ወደፊት ይህ እንደሚከሰት መገመት እንዴት ተሳናቸው?የሚሉም አሉ። በወቅቱ የነበሩት እነ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፤ ንቡረ እድ መኩሪያ፤ የመሳሰሉት ሊቃውንት ጵጵስናው በመንኩሰና ላይ ተመስርቶ እንዲመጣ ቢስማሙም ሳይፈትሹና ሳይመረምሩ ያለገደብ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አልጫኑት ነበርና በዚህ አጋጣሚ ያባቶቻችንን አርቆ አስተዋይነታቸውን ሳንመሰክርላቸው ልናልፈው አይገባም።

ጵጵስናው በግብጻውያን ልማድ በመነኩሴ ይቀጥል ወይስ በመአስባን ማለትም በተቀደሰው ህጋዊ ጋብቻ ከተወሰኑ ሊቃውንት መካከል በሞራሉ በታማኝነቱ በእውቀቱ የተሻለ የተመረጠ ይሁን? የሚለውን ሀሳብ አንስተው ንግግራቸውን በቀኖናው ላይ መስርተው ተወያይተውበት፤ ተከራክረውበት እንደነበረ ከመምህሮቻችን ሰምተናል።

በመአስባን ትክክ ላይ ይረፍ የሚለው ቡድን ንግግሩን "ኢይደልዎ ለመናኒ ከመ ይፍቱ ሢመተ ክህነት ወኢሊቀ ምኔት ።እስመ ፍቅረ ሢመት ደዌ ሰይጣናዊ ውእቱ ወዘወድቀ ውስተ ዝንቱ ሕማም ይከውን ቀናኤ ላእለ እለ ይደልዎሙ ከመ ይኩኑ ካህናተ ወሥዩማነ ወይቀጽብ ሰብአ ላዕሌሆሙ። ወያስተናስእ ወየሀስስ ሞቶሙ ከመ ይኩን ውእቱ በመዓርጊሆሙወሶበ ኮነት ሎቱ ኢንኢድ ይከውን ማእከሌሁ ወማእከሊሆሙ ሁከት" (ፍ .አን 10፡385) በሚለው ቀኖና ላይ

አንተርሶ በጋብቻ ከተወሰኑት ከሊቃውንቱ መካከል በጥንቃቄ ተመርጦ እንዲሰየም ተከራከረ።

የግእዙ ትርጉም "መነኩሴ ወደ ሹመት ወደ አበ ምኔትነት አይቅረብ። ልቡን ይነሳዋል ህሊናውን ያደነዝዘዋል። በሰዎች ላይ ያየው ሁሉ ዓለማዊ ነገር ያስቀናዋል። ያሰክረዋል። ያሳብደዋል። ከሱ ይሻላሉ ብሎ በሚገምታቸው ሊቃውንት ላይ አድማ እየቀሰቀሰ ያስገድላቸዋል። በህብረተ ሰቡ መካከል ጸብ እያነሳሳ ህውከት ይፈጥራል" የሚል ነው።

በተቃራኒው እንደ ግብጻውያን በምንኩስና ላይ ይቀጥል የሚለው ቡድን "ወህዝባዊ ያስተህምም በነፍሱ አንተሰ ጾርከ ጾረ ከቡደ " (ፍ አ 5፡120) በሚለው ቀኖና ላይ ክርክሩን መስርቶ በተቀደሰው ጋብቻ ይሁን የሚለውን ተቃወመ።

የግእዙ ትርጉም፡- ሲብራራ ፡- በትዳር በልጅ የታሰረ ትኩረቱን መሰብሰብ ያዳግተዋል። መጽያትን እንዳያይ ይጋርደዋል መስዋእትነት የሚጠይቅ ሲከሰት ልጄን ቤቴን የሚለው ተጽእኖ ያዘናጋዋል። መነኩሴ ግን ለህዝብ ተላልፎ ለመሞት ሲል አስቀድሞ ከህግ ጋብቻ ራሱን ገድሏል። ከትዳር ከልጅ እስራትና ከገንዘብ ከጥሪት ፈጽሞ የራቀ ስለሆነ በህዝብ ላይ የሚመጣውን መከራ ከህዝቡ በፊት ይጋፈጠዋል። በህዝብ ላይ ሚመጣውንም ሞት ከህዝብ በፊት ይሞታል ስለዚህ መነኩሴ ይሻላል" በሚለው ተስማሙ።

አባቶቻችን ሊቃውንት ጵጵስናን በምንኩስና ላይ እንዲቆይ ሲወስኑም፡- ትዳር በሚያስከትለው ሀላፊነት ላይ የጵጵስናው ሀላፊነት ተደርቦ ተልእኮው እንዳይደከምና ስርአተ አልበኝነት እንዳይከሰት እንጅ፤ በኦርቶዶክስ ስነ መለኮት አንድምታ ከማጥመቅና ከማቁረብ በላይ ቅዱስ የሆነ በክህነት የማይፈጸም ሌላ ተልእኮ እንደሌለ የተገለጸ ነው። በሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግንዛቤ ከተቀደሰው ከጋብቻ ቅድስና በላይ፤ የምንኩስናን ቅድስና ከፍ በማድረግ አልነበረም።

"ኢያንበብክሙኑ ከመ ዘፈጠሮሙ እምትካት ብእሴ ወብእሲተ ገብሮሙ። በእንተዝ የኅድግ ብእሲ አባሁ ወእሞ ወይተለዋ ለብእሲቱ ወይከውኑ አሀደ ሥጋ" (ማቴ 19፡4) ብሎ ክርስቶስ በስነ ተፈጥሮ ቀድሶ ጋብቻን እንደሰራው

ያስተማረውን የጋብቻን ቅድስና የኦርቶዶክስ ስነ መለኮት አስተምህሮ ከምንኩስና ቅድስና በታች ዝቅ አያደርገውም።

"ምንኩስናሰ እምፈቃድ ይእቲ ወአኮ በግብር" (ፍፍ አ 10፡ 350) ማለትም፡- ምንኩስና የግለሰቡ ምርጫ እንጅ በህገ ተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ አይደለም" ሲብራራ ምንኩስና ተአምርና ገድል በሚያሰራ በልዩ ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ካልጠራው በቀር ማንም ሊገባበት አይፈቀድም። ከገባበት በኋላ መሸከም ካቃተው ወደተቀደሰው ትዳር ቢገባ፤ ልቀድስ ልባርክ ካለለ "የጋብቻን መፍረስ እጠላለሁ" (ሚል 2፡15__16) የሚለው አምላክ የምንኩስናን መፍረስ እጠላለሁ አላለም። ይልቁንም በትዳር ይወሰን ነው የሚለው።

አባቶቻችን በዚህ ውይይት ተስማምተው በተጠቀሱት ምክንያቶች ጵጵስና በመነኩሴ ላይ እንዲሆን ሲስማሙ ያለ ገደብ በህዝብ ላይ አልለቀቁትም። "ወኢይግባእ ኀበ ድህር ወከመ ይፈጽም ትእዛዞሙ ለሊቃውንት ዘለሊሁ ወይህሥሥ ዘይደሉ ለመድሀኒተ ነፍሱ" (ፍ አ 10፡ 346) በሚለው ቀኖናዊ መርሆ ማለትም ፡- ጵጵስና ከምንኩስና ርቆ በፈቃደ ሥጋው ተሸንፎ በሥጋ ዘመድ፤ በቡድን፤ በመሳሰሉት ሸቀጣ ሸቀጥ ሀሳቦች ተገዶ የህዝቡን ዋይታ ማዳመጥ ችላ ቢል ሊቃውንቱ ይገስጹት ።

የሊቃውንቱን ተግሳጽ የማይቀበል ከሆነ ፡-"ወይቁሙ ላዕሌሁ ካህናቲሁ በጽድቅ ዘይደሉ፤ ይትዐደው ኀበ አባግዓ ክርስቶስ ዘተሤየጦሙ በደሙ ወኢያስተቁጥኦሞ ወኢያብጽሆሙ ሀበ ዕረፍት ላእለ እግዚአብሄር ወክህደ ህጎ ቅድስተ። ወኢይኅድግዎ ይንበር ላዕለ ፍትህ ወኢየአዝዝ በሲመቱ ወኩን መሃይምነ እንዘ ይትዌከፍ ግፍዖ በሠናይ ከመ ዘይደሉ ለእሌሁ" (ፍ አ 5፡182__185) ። በሚለው ቀኖናችን መሰረት ወዲያውኑ ከመንበሩ ያባሩት የሚለውን ገደብ እንደሰሩለት ከመምህሮቻችን ሰምተናል።

ጳጳሱ በማወቅም ባለማወቅም ሲሳሳት፤ ወይም በዝምድና በቡድን ተሸንፎ ህዝብ ከሚበድለውና ከሚያሳድደው ጋራ ሲስማማ፤ "መሐርዎሙ ለእለ የሐውሩ ዘእንበለ አዕምሮ ወለእለ ተምህሩ አጽንእዎሙ ወሚጥዎሙ ለስሁታን ወንግርዎሙ በኩሉ ጊዜ በእንተ ስህተቶሙ" ( 5፡ 117) በሚለው ቀኖናችን ሊቃውንቱ መገሰጽ እንዳለባቸው ከማስጠንቀቂያ ጋራ እንጅ፤ ጵጵስናን ከግብጽ አላቀው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ሲያደርጉ በህዝብ ላይ በመረን እለቀቁትም። አባቶቻችን

ጵጵስናን ከግብጻውያን ነጥቀው ለአገር ልጅ በአደራ ሲሰጡ ለቀጣዩ ትውልድ የነበራቸው አርቆ አሳቢነትና ጥንቃቄ  እጅግ የሚደነቅ ነውና ሊወደሱ እንጅ ሊወቀሱ አይገባም።

ከሲኖዶስ አመራር በፊት በነዚሁ ሊቃውንት አባቶቻችን ጥብቅ ቁጥጥር ይመራ የነበረውን መንፈሳዊ አመራር ይመለከቱ የነበሩት የአኀት አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንት ፤ በተለይም ግብጾች በጋለ ስሜታቸው ይመኙት እንደነበረ Haggai Erlich የተባሉ ደራሲ (the cross and the river page 68) በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው "In time this modern wing of the Coptic community would develop  its own Ethiopian ideas, quite ddifferent from those of the patriarchet, the Holy Synod, and the Coptic Church establishment" ብለው መስክረዋል።

እነ ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሤ፤ እነ ብላታ ምርስኤ ሐዘን ወ/ ቂርቆስ፤ እነ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፤ ንቡረ ዕድ መኩሪያ የመሳሰሉ አርቀው የሚያስቡ አባቶቻችንን አፍርታ የነበረችው ቤተ ክርስቲያናችን፤  ካንድም ሁለት ፓትርያርኮች ከ60 በላይ ጳጳሳት በሚተራመሱበት ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ የተደራረበ የመከራ አይነት በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ ዘነበበት። ለሕዝብ ተላልፎ የሚሰዋ ይቅርና ቤተ ክርስቲያን ከመቃጠሉ ህዝብ ከመታረዱ በፊት ካራጁ ጋራ እየተናበብን ህዝቡን ለመከራ ንዋየ ቅድሳቱን ለእሳት እየዳረግን ወደ አዲስ አበባና  እሳቱ ወደማይደርስባቸው ቦታወች  በረገግን።

በገጠር ያሉ ብዙ ቀሳውስት  ከህዝቡና ከነዋየ ቅድሳቱ ጋራ ተቃጥለዋል። ክብሩን ጥቅሙን ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋራ እየተወዳደርን በመሻማት ላይ ያለን እኛ ግን ከጥቂቶች በቀር በተሰየምንበት ቦታ ጸንተን አልቆምንም። እሳቱ በማይደርስባቸው ቦታወች ያለን ብንሆንም ከጥቂቶች በቀር የት ጠፉ እንዳንባለና አለን ለማለት ብቻ  የመከራው ግለት በህዝቡ ላይ ነዶ በረድ ሲል ብቅ እያልን አንዳንድ ቃል ጣል እናደርጋለን ። በሙሉ ስሜታችንና አካላችን  ከህዝቡ ጋራ ግን የለንም።  የግብጹ ዜጋ አቡነ ቄርሎስ ጥለው በመሸሽ ከፈጸሙት በደልና <u>ክህደት ይልቅ፤ በዚህ ዘመን ባለው ፓትርያርካዊ አመራር ስር ያለን ሁላችን የፈጸምነው በደልና ግፍ እጅግ ገዝፎ እየታየ ነው።</u>

በጊዜው በነበሩት የፖለቲካ ባለስልጣናት ከአሜሪካ ተጎትቶ በመንበሩ ከተቀመጠው ፕትርክናዎና  ባንድ ወቅትም ፕትርክናዎ እንደመሰከረው በብር

እየገዙ የገቡ ሁሉ በሰላምና በተረጋጋ ዘመን ከአገራችን ሊቃውንት በላይ ብሩን ንብረቱን ክብሩን ሲዘርፉ ኖረው በመከራ ጊዜ ጥለው ከኮበለሉት አቡነ ቄርሎስ ባሱ እንጅ በምን ተሻሉ? እንዲያውም በህዝቡ መካከል ቁጭ ብለው እየበሉ እየጠጡ የህዝበ ክርስቲያኑን መጨፍጨፍ እያዩ ከወያኔ ጋራ በመተባበር ታራሚ እያሉ በህዝብ ላይ ያልተሳለቁት ጥለው የሄዱት አቡነ ቄርሎስ በብዙ ነገሮች ይሻላሉ' የሚል የምሬት ቃል በሰፊው እየተሰማ ነው።

## 5ኛ፡-በአቡነ ቄርሎስ ያልፈረሱ በኛ ብዙ ነገሮች ፈረሱ

አቡነ ጴጥሮስ በአውደ ምህረቱ ላይ ስለ ህዝባቸው በአንደበታቸው የሰጡት ምስክርነት ባያረካቸው በደማቸው ጠብታ ምድርን እንድትመሰክር አስገደዷት። ኢትዮጵያ ብሶቷን ለምትናገርባቸው ጃን ሜዳንና መስቀል አደባባይን ለመሳሰሉ መገናኛወቿ በህውልታቸው ተጨማሪ social meadia ፈጠሩላት።

ዛሬ በተግዳሮት ላይ የወደቁት ጃን ሜዳና መስቀል አደባባይ ኢትዮጵያ ለአውሮፓውያን ወራሪወች የተግሳጽ መፈክር መልእክታት የምታስተላልፍባቸው በየደብሩ ላሉት አውደ ምህረቶች ተጨማሪ social meadia ነበሩ። ዛሬ አደባባዮቻችን ባድማ ሆኑ። በየአደባባዮቻችን ይተላለፉ የነበሩት ጽድቅም መደመርም መልእክቶቻቸውን ሳቱ።

## 6ኛ፡-የታፈነው ጃን ሜዳና መልእክቱን የሳተው ጥምቀት

በጃን ሜዳ ይተላለፍ የነበረው መልእክት ክርስቶስ ሲጠመቅ "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባና" የሚለው የክርስቶስ አዋጅ ነው። ሊቃውንት አባቶቻችን እንዳስተማሩን ክርስቶስ በጥምቀቱ ያወጃት ጽድቅ በመንግስተ ሰማይ ባለችው ጽድቅ ብቻ የምትወሰን አይደለችም።

"ፍትሕ ወርትዕ ተድላ መንበርከ ሣህል ወጽድቅ የሐውር ቅድመ ገጽከ" 88፡ 14 እንዳለው ጽድቅ ይቅርታ ፍትህ ርትዕ የአምላክ ባህርያት ናቸው። እግዚአብሔር ያየናል የሚሉ ሁሉ ከነዚህ ባህርያት ሊርቁ አይገባም። ክርስቶስ ሲጠመቅ "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባና" ያለው ይህን ሁሉ የሚያካትት ነው ብለው መምህሮቻችን ያስተምራሉ።

ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ካሉት አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መንገድ በጥምቀት በዓል አሰርቱ ቃላት የተጻበትን ጽላት ተሸክማ ወደ አደባባይ

የምትወጣው "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም አለብን" ብሎ ጌታችን ያወጀውን ምሥጢር ለማወጅ ብቻ አልነበረም። እንዲህ ነበር ብለን ያለፈውን ክርስቶስ ሲጠመቅ የተከናወነውን እንደ ድራማ ለማሳየት ወይም ዓመታዊ ልማድ ለማድረስ ብቻ አልነበረም። ችግር እየፈጠሩ የሚጣሉትን ያገር ልጆች እያስታረቁ፤ ከውጭ የሚመጡትን ወራሪወች እየገሰጹ የሚያባርሩበት መንፈሳዊ ኃይላቸው ጭምር ነበር።

በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን አጎራባች አገሮችን ወረው በማሰቃየት ይገዟቸው የነበሩት አውሮፓውያን የተጠመቁ ክርስቲያኖች ነበሩ። ግን የተጠመቁበትን ምሥጢር ከደው የሰው አገር የሚወሩ አረመኔ አስመሳዮችና ሽፍጠኞች ነበሩ። አባቶቻችን ሊቃውንት እነዚህን አስመሳዮች "ክርስቲያኖች አይደላችሁም። ክርስቲያን ልትሆኑ ይቅርና "ኢትትኀለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርኡ አበዊከ በውስተ ርስትከሙ " (ዘዳ 19፥12) ብሎ ከሚያዝዘው ከኦሪቱ ያልደረሳችሁ አረመኔወች ከህገ ኦራዊት ያልተላቀቃችሁ ናችሁ" እያሉ ይግስጹበት ነበር።

"በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል። ሕግ በሙሴ ተሰጥቶን ነበር። ጸጋና ጽድቅ ግን በኢየሱስ ልርስቶስ ሆነልን" (ዮሐ 1፥17) የሚለውን የክርስቶስን ፈቃድ የገሰሳችሁ ናችሁና አትጠጉን" እያሉ የውግዘት ቃላቸውን ያስተላልፉበት ነበር።

ክርስቲያኖች ብትሆኑ ኖሮ "ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም "(ማቴ 5፡20) ብሎ ያስተማረውን የክርስቶስን ቃል ክዳችሁ የሰው አገር አትወሩም ነበር። ክርስቶስ "ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል" ብሎ ያወጃትን ረስታችሁ የጽድቅ ተቃራኒ የሆኑትን ተግባራት በመፈጸም ላይ ስላላችሁ የሚያቃጠል እሳት የተዘጋጀለት ገለባወች ሆናችሁ። የሚቆርጥ ምሳር በአንገታችሁ የተሰነዘረባችሁ ግንዶች ናችሁ" እያሉ ሊቃውንት አባቶቻችን መፈከራቸውን ለወራሪወች ያሰሙበት ነበር።

አዛውንቱ ወጣቱ ኢትዮጵያውያን " የፍትህ የጽድቅ ምንጭ ለሆነው ሆ ! በል" ማለትም ታዘዘው ስማው ! የትእቢተኞችን አለቃ ዲያብሎስን እምቢ በል ! (2ኛ ጴጥ 4፡8) የሚለውን የቅዱስ ጴጥሮስን ትምህርት መነሻ በማድረግ በታቦተ ህጉ ዙሪያ በሚያቀልጡት ሆታቸው ግርማና ሞገስ ለተመላው ትእይንት መድረክ ነበር። ከዚህ ቀጥለን መስመሩን የሳተው መስቀል አደባባይንና ትርጉሙ የተቀየረውን የመደመርን መልእክት እንመልከተው።

## 7ኛ፡-የታፈነው መስቀል አደባባይና ትርጉሙ የተቀየረው ደመራ

በጃን ሜዳ ላይ በጥምቀቱ በዓል የሚተላለፈው መልእክት፤ በደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ ከሚተላለፈው መልእክት ጋራ ተመሳሳይ ነው። በታሪክ እንደተመዘገበው የደመራን በዓል የጀመረችው በመካከል ምሥራቅ እሌኒ ናት። እሌኒ የመስቀሉን ታሪክ በሰራችበት ቦታ እኛ ደመራ የሚል ድርብ ስም ሰጥተን በምናከብርበት ሁኔታ ሊከበር ቀርቶ አይታወስም።

የጥምቀቱን በዓል በጃን ሜዳ የምናከብረው ክርስቶስ ሲጠመቅ የተከናወነውን ለማሳየት ወይም ዓመታዊ ልማድ ለማድረስ ብቻ አንዳልነበር ሁሉ፤ በመስቀል አደባባይ የምናከብረውም ከእሌኒ ጋራ የተያያዘውን ታሪክ ወይም ወደኛ ተሻግሮ መጣ የምንለውን የግማደ መስቀሉን ታሪክ ለማስታወስ ብቻ አይደለም።

”ደምረነ ምስለ እለ ይድህኑ“ ምስለ ደቂቀ ብርሃን ማለት፡- ኃላፍያትን ከማይዘነጉ በፊታቸው ያለውን ከሚያስተውሉና መጽያቱን ከሚመረመሩ ኃጢአታቸው ባስከተለው መቅሰፍት ከማይጠፉ ጥበበኞ ጋራ ደምረን“ የሚለውን የየእለቱ መመሪያችን እናደርገው ዘንድ በጸሎት መልክ እንደግመው ነበር። አባቶቻችን አጎራባች አገሮችን የወረሩት ቅኝ ገዥወች ወያኔወች እንዳደረጉት ህዝቡን ለመከፋፈል ድንበር እየጣሱ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት የሚፈጽሙትን ደባ ህዝብ ነቅቶ እንዲከላከል የማስጠንቀቂያ መልእክት ነበር።

Haggai Erlich የተባሉ ደራሲ ከሲኖዶስ በፊት ነበረውን ያባቶቻችንን መንፈሳዊ አመራር ምሥራቃውያን ሊቃውንት ይመኙት ነበረ እንዳሉት፤ ለተገፉት ነጻነት ይታገሉ የነበሩት ምዕራባውያኑ ሊቃውንትም ኢትዮጵያውያን አንድነታቸው ፈርሶ እንዳይከፋፈሉ ያስተምሩበት የነበረውን የደማራን መልእክት፤ cultural theology በማለት ያደንቁታል።

ምዕራባውያኑ “Liberation theology calls the affluent of the world not only to stand in solidarity with the poor and the oppressed , but ultimately to become like Christ the Lord, who for our sake he became poor, so that by his poverty we mught become rich (2 Corintians 8; 9) (Liberation Thelogy page 16) በማለት ለታገሉት መንፈሳዊ ተጋድሎ፡ አባቶቻችን ምሳሌ መሆናቸው እጅግ ያኮራናል።

“ወእምተደምሮ በዕልወት ወርኩስ ምስለ ዓላውያን ወአረማውያን” ማለትም፡- በክህደት በህሊና ጠለሸት ከተበከሉት አረመኔወች ጋራ ከመደምር አድነን“ በሚለው ቀኖናችን መሰረት አንዳችን ባንዳችን ላይ ከለጠፍነው ጽቡረ ኃጢአት ባልተነካካ ተገቢ ቅዱስ አባት ጸሎተ ቡራኬ ነጽተን ባለመደመራችን በህዝባችን ላይ የሚነደውን እሳት አስከተለ።

“ንሁር ፍኖተ ርትእተ እንተ ኀቤሃ መርሖነ አበዊነ ንጹሐን ወይእቲ ትወስደነ ሕይወት ዘበአማን ። ወእሉሰ ኅጡአነ አዕምሮ እለ አጽለሙ ብርሃናተ ብርሃን ኢተምህሩ ወኢያእመሩ አእምሮ ሃይማኖት ዘነበብናሁ ንህነ“ 97፡ 19 ማለትም፡- መደመሩ በፖለቲካዊ ቀመር እምነታችንና ቀኖናችን ባልተገነዘበና ባላገነዘበ ስልጣን ሽምግልና ተደረገ እንጅ ንጹሀን የቀደሙ አባቶቻችን ባስተማሩን ወደ እውነተኛዋ እርቅ በምታደርሰን ትውፊት ባለመፈጸሙ “ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ካዷት ኢትዮጵያንም ትፏት የሚል ከቀድሞው ክፋትና በደል የከፋ እጅግ የሚዘገንን ድምጽ ተሰማ። ከዚህ በታች በተቀመጠው ቀኖና መደመሩ ቢፈጸም ኖሮ፤ ካንድ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ኢትዮጵያን ትፏት የሚለው ቃል ባልተሰማ ነበር።

የሳትነውን መመሪያም ተርጉሜ የማቀርበው ግእዙን ልጥቀሰው። “እስመ ኩልነ አህደ መንፈሰ ሰተይነ ወአህተ ጥምቀተ ተጠመቅነ ወአዲ እቅፍት ውስተ አልባቢክሙ በእንቲአነ ዘይዘርዕ ሰይጣን ርጉም . . . . . እለ እሙንቱ አርጋኖነ ዲያብሎስ ርጉም እሉ እለ ያማስኑ ህሊናተ ርቱአተ ወጽሩያተ እስመ ንህነ ሀሎነ በሃይማኖት ርትዕት ወብርህት ወጽድቅት“ ሰአልወሙ ለኩሎሙ ቅዱሳን እለ ሀለው መንገሌክሙ ቅሩባነ ወርሁቃነ ይጸልዩ ወያስተብቁዑ በእንተ ድካምነ ወበእንተ ቤተ ክርስቲያንሂ ኦርቶዶክሳዊት እሞሙ ወሐጻኒቶሙ እስመ ጽድቅ በኀቤነ ከመ እግዚአብሔር ኢያስተሀፍሮሙ ዘይጼውኦ በልብ ንጹህ ወይሁቦ ስእለቶ ለዘጸለየ” 102፡39__41)

<u>ሲተረጎም፡-ሁላችንም አንዲት ጥምቀት ተጠመቀናል። አንዲትን መንፈሰ ህይወትም ጠጥተናል። በዲያብሎስ የሚቃኙ የተረጉሙ የዲያብሎስ ልጆች የቀናውን የጸዳውን ህሊናችንን እንዳያጎድፋብንና ሌላ ውድቀት እንዳይገጥመን በቀኖና በስነ መለኮት ላይ የተመሰረተው ጽኑ እምነታቸው ባልተናወጠባቸው በረከስንበት ጽቡረ ኃጢያት ያልረከሱ አባቶችን ጥሯቸው ጋብዟቸው በንጹህን አበው የሚቀርበውን ጸሎት የሚቀበል አምላክ የነሱን ጸሎት ተቀብሎ ከረከስንበት</u>

እንደሚያጸዳን እናምናለን“ የሚለውን ዘነጋነው ። እርስ በርስ እኛው በኛው ተሻሽን እንጅ ከተበከልንበት ባለመጽዳታችን አንዲት ጥምቀት የጠመቁትን። አንዲትን መንፈስ ህይወትም የጠጡትን አርቶዶክሳዊይንን እርስ በርስ ከመጨራረስ ልናተርፋቸው አልቻልንም።

ያባቶቻችን አንድምታ “ኢታስተጻምር አድገ ወላህመ ኅቡረ ከመ ትሕርስ፤ዘዳ 22፥10) በሚለው በኦሪቱ ጀምሮ ”ኢየሀሉ ተኩላ ምስለ በግዕ አንቄ ምስለ ርግብ ክርዳድ ምስለ ሥርናይ“ (አ ገጽ 216) እያለ በስርአተ አምልኳችን (liturgy) የሚደመድም ነው።

ኦሪቱ “አህያንና በሬን አንድ ላይ ጠምደህ አትረስ” ብሎ የሚሰጠውን ትእዛዝ ስርአተ አምልኳችን “በግንና ተኩላን፤ ርግብንና ጭልፊትን ስንዴንና እንክርዳድን አትደምሩ” ብሎ ያጎላምሰዋል።

ኢትዮጵያ አትፍረስ ህዝብም አይሰቃይ እያሉ ሲታገሉ የኖሩት ወገኖች፤ ህዝብ በገጀራ እንዲታረድና እትዮጵያ እንድትፈርስ ሲጥሩ ከነበሩት ሰወች ጋራ ተደምረው ሲታሰሩ አለመቃወም፤ የመደመር ትርጌሜ መፋለሱን የሚያሳይ ነው

“ወእምኩሉ ግዘት” እንዲል መጽሐፋችን በቅዱስነተዎ አመራር ያለን ሁላችን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን የመሳሰሉ የቀደሙ አባቶቻችን ካወገዙን ውግዘት ባለመፈታታችን ከተቀመጠንበት ተነስተን ከቆምንበት ተንቀሳቅሰን ህዝባችንን ከመከራው እንዲወጣ ልንደርስለት አልቻልንም።

ክፉ በሚያስቡ ግለሰቦች ወይም የህብረተ ሰብ ክፍሎች ተጭሮ በመላ ኢትዮጵያውያ ላይ ሲነድ የኖረው እሳት ”ወበልአቶሙ እሳት ለወራዙቶሙ ወኢለህዋ ደናግሊሆሙ ወካህናቲሆሙኒ ወድቁ በኲናት። ወኢበክያ ዕቤራቲሆሙ“ (መዝ 77 ) እንዲል፡- ዛሬ በኢትዮጵያውያን ጎልማሶች በወጣት ወንዶችና ሴቶች፤ በካህናቱና በእናቶች ላይ ሲነድ ተቀምጠን በመሞቅ ላይ እንዳለን ዓለም እያየን ህዝባችንም እየታዘበን ነው።

እስካሁን የገለጽኩት የደረሰብንን መከራና፤ መከራውን ለማስወገድ ያልተጠቀምንበትን የቤተ ክርስቲያናችንን መንፈሳዊ ኃይል ነው። ከዚህ ቀጥየ በቅዱስነተዎ አመራር ሊደረግ ይገባል ብየ የማስበውን ለማቅረብ እኖክራለሁ።